*ቀን: መጋቢት 22/2002 ዓ.ም.*

# "የአዛኝ ቅቤ አንጓች"

*ከፀሐዬ ደባልቀው*
*ዋሽንግተን ዲሲ*

የኢትዮጵያ ሕዝቦችና ብሄር ብሄረሰቦች የመብታቸው አንጓ፣ የእኩልነታቸው መሠረት፣ የህልውናቸው ደንደስ፣ የልማታቸው የማዕዘን ድንጋይ፣ የአንድነታቸው ዋስትና፣ የጋራና የግል ሕልውናቸው ድል የሆነውን ሕገመንግሥታዊ፣ ዲሞክራሲያዊ የፌዴራልና የክልል ም/ቤቶች ፓርላሜንታዊ ክንውን በምርጫ ሰሞን የይሁንታቸው ማህተም ለማስፈር ወደ ውሳኙ የግንቦት 15 ቀን 2002 የምርጫ እለት መዳረሻ መንገዳቸው ላይ በመሰምሰም በአንድ ልብ፣ በአንድ ዕምነትና በአንድ ቃል የወሳኝነት ብይናቸውን በማያዳግም ፍትሃዊ መልኩ ለመስጠት እጅ ለእጅ ተያይዘው ወደፊት በመትመም ላይ ናቸው::

ይኸንን ታሪካዊ ጉዞ የሚያደርጉት ተገቢውንና አስተማማኙን፣ የልማት፣ የዲሞክራሲ፣ የፍትህ፣ የመልካም አስተዳደርና የሰላም ስንቅ ቋጥረው በነገይቱ ኢትዮጵያ ለሚወስዱት እመርታ እርምጃ እርሾና ዘር በእርግጠኝነት ያስጨበጣቸውን መሠረት በብረትና በሲሚንቶ መርገውና ለስነው በመንፈስ ሙልዕነትና በልበ ደንዳናነት በመገስገስ ነው:: በአንፃሩም የሕዝብ ወሳኝነትና ሰላማዊና ዲሞክራሲያዊ ጉዞ ከቶውኑ የማይጥማቸው አንዳንድ ወገኖች ከውስጥና ከውጭ በአልሞት ባይ ተጋዳይነት መንፈስ ተፈላልገው ከሩቅና ከቅርብ በእኔ ከሞትኩ ሣር አይብቀል ብሂል ተጠራርተው ያለ የሌለ ኃይላቸውን በማስተባበር በግብዓተ መሬት የመጨረሻው ሴኮንድ የመፍጨርጨር ስሜት ተገፋፍተውና በመቃብር አፋፍ ላይ ተወጥረው ያዙኝ ልቀቁኝ በማለት ትንፋሻቸውን አምቀው በፍፃሜው የአልሞት ባይ ተጋዳይነት ከንቱ መፍጨርጨር በማድረግ እየተውተረተሩ ይገኛሉ::

በሃገር ውስጥ የበግ ለምድ የለበሱ ተኩላዎችና ሕጋዊ ሽፋን የተላበሱ አቀንቃኞቻቸው ልዝብና መሰሪ ተልዕኮአቸውን እውን ለማድረግ በማር የተለወሰ መርዝ ለውሰው ለሕዝቡ በማቅረብ ከውጭ ለያዥ ለገራዥ በሚያዳግት መልኩ ቁና ቁና በመተንፈስ መጣንልህ መድህኖችህ እኛ ነን በማለት የአዞ እንባ እያነቡ ሕዝቡ ባለፉት 20 ዓመታት እልህ አስጨራሽ ትግልና ወሰንየለሽ ሕዝባዊ ትዕግስትን ተላብሶ በእጁ ያስገባውን በዓይኑ በብረቱ የሚያየውን የሚዳስሰውንና የሚጨብጠውን ግዙፍ ሁለንተናዊ ልማታዊ ውጤት፣ የእንቧይ ካብ፣ የንጋት ጤዛ፣ የሚተን አየርና በአሸዋ ላይ የተገነባ ድርቡሽ ነው በማለት እያጣጣሉ መልከ ጥፉን በስም ይደግፉ እንዲሉ የሴሚናር ዓይነት፣ የኮንፈረንስ ጋጋታ፣ በመብት ተሟጋችነትና በነፃነት ጠበቃነት እሩምታ በአንጉል ስሞች ያሸበረቁ አስመሳይ መፈክሮች ያጌጡና ከእኛ በላይ ላሳር በሚል ምፀታዊ ግብዝና በመኮፈስ በምሁራን ተብዬዎች የታጨቁ አያሌ መድረኮችን በኢትዮጵያ ሕዝብ የመብትና የነፃነት ማስጠበቂያ ስላቅ በቃረሙት የእርጥባን ንዋይ በማሰናዳት የሕዝቡን ብይንና ሰላማዊ የትግል አቅጣጫን ለማደፍረስ የፈላ ውሃ ቸልብሰው ፈሩን ስቶ እነሱ በእናውቅልሃለን ፈሊጥ ወደ ደገሱለት የማያባራ ጦስ ሰተት ብሎ እንዲገባላቸው የማይፈነቅሉት አለት፣ የማይቀነጥሱት ቅጠል፣ የማይጎነጉኑት ሸርና የማይሸርቡት ሴራ የለም::

ለቀባሪ አረዱት እንዲሉ እነሱ በሺዎች ኪሎ ሜትሮች በሚሰላ ርቀት ላይ በአውሮፓና በአሜሪካ አማላይና ውብ ከተሞች በኢትዮጵያ ሕዝብ ስም የዚህ ትግል፣ የዚያ መብት አራማጆች ነን በሚል እየቀላመዱ ከከበርቴው ሥርዓት በሳ አድራጊዎችና የናጠጡ አትራፊ ያልሆኑ ድርጅቶች በሚወረወርላቸው ፍርፋሪ የተደላደለ ኑሮአቸውን እየቀጨና፣ ከየዋሁ ብዙሃን ኢትዮጵያዊ የዲያስፖራው ሕብረተሰብም በሰበብ አስባቡ እጁን የመጠምዘዝ ያህል የስነልቦናዊ ጦርነት፣ የሥም ማጥፋት ዘመቻና እንዲያም ሲል የሽብርና የማስፈራሪያ አዘል ኘሮፖጋንዳ በታጀበ ውትወታ እርቃኑን በወጣ የለየለት ውሸትና ኢትዮጵያና ሕዝቦችዋ በዝንተ ዓለማዊ የጭለማ ግርዶሽ ውስጥ እንደተዘፈቁ በሚያስመስል ጽልመታዊና ዘረኛ ቅስቀሳና በሬ ወለደ ነጭ ውሸት ላይ በመንተራስ በሚሰበስቡት ገንዘብ ባህላዊ መደብሮች፣ ምግብ ቤቶች፣ ጋዝ ስቴሽኖች፣ ሱቆች፣ የሚከራዩ ቤቶችና ልዩ ልዩ አገልግሎት ሰጭ ተቋማትና ታክሲዎች፣ እንዲሁም የመኪና ማገቻ ሥፍራዎች /Parking Lots/ በፈረደበት የኢትዮጵያ ሕዝብ ስም የመብት አስከባሪነት፣ የሰላም ተቆርቋሪነት፣ ነፃ አውጭነትና የዲሞክራሲ ተሟጋችነትና የሕዝቡ ጠበቃነት የንግድ ታፔላ ለጥፈው ብዙሃኑ ኢትዮጵያዊ ዕረፍት አጥቶ በሚባዝንበት ከእጅ ወደ አፍ በሆነ በየሃገሮቹ ስታንዳርድ በሚንጠራወዝበት ኑሮ እነሱ የተንደላቀቀ ኑሮአቸውን ይገፋሉ::

ይኸንን አኩይ ነገር ግን ለራስ ሲቆርሱ አያሳንሱ እንዲሉ ለራሳቸው የምድር ገነት ያጎናፀፋቸው ንግዳዊ ፖለቲካዊ ብልጣ ብልጥነት የዘወትር ሰለባ ሆኖ ይቀጥል ዘንድ ብዙሃኑ ኢትዮጵያዊ ስደተኛ እርስ በርሱ በመፈራራትና በመጠራጠር በጠላትነት በጎሪጥ እንዲተያይ፣ ስለሃገሩ ለአፍታም ቢሆን በጎ ነገር እንዳይሰማ፣ በዘርና በዕምነት እንዲቦጫጨቅ መርዛም የከፋፍለህ ግዛ ሴራቸውን እየፈተሉ የእነሱ የዘለዓለም ላሜ በራ ሆኖ እንዲታለብላቸው ሳይታክቱ ሌት ተቀን የተንኮል መርዛቸውን ይረጩበታል።

ይኸንን መጣጥፍ ሳቀርብ ሰሞኑን በውስጥና በውጭ በቅብብሎሽ የተቀናጀና የተደራጀ ፀረ ኢትዮጵያ ጩኸት የበረከተበትን መስጢር ለማጤን እንደመንደርደሪያና ዓይን ግላጭ መግቢያ በመሆን በእያንዳንዳችን ህሊና ሁነኛ ጥያቄን አጭሮ ልቦናችንን ከፍተን አዕምሮአችንን ብሩህ በማድረግ መልሱን በማፈላለግ አንድንተጋ እርሾ ይሆነን ይሆንወይ በማለት ነው። በተረፈ በዚህ ጽሁፍ አጠቃላይ መንደርደሪያ ሰሞኑን በአካባቢያችን ከአፅናፍ እስከ አፅናፍ ለሰሚው እስከሚሰለች ድረስ እየተለፈፈለት ስላለው "የመልካም አስተዳደር ፣ ሰላም፣ ደህንነት እና ቀጣይ ልማት በአፍሪቃ ቀንድ" በሚል ርዕስ ስር ከApril 9-11/2010 ለሦስት ቀናት በ"Double Tree Hotel" Arlington Virginia ላይ ይካሄዳል በሚል ሰሞኑን ኢንተርኔት ላይ ስጎረጉር ቀልቤን ማረከውና አዘጋጆቹን Advocacy for Ethiopia and Ethiopian National Priorities Consultative process የሚል ካባ መደረባቸውን ስገነዘብ ለመሆኑ በዚሁ የምሁራን መድረክ የሚቀርቡትና ጥልቅ የተባለላቸው የምርምር ጽሁፎችን የሚያቀርቡት እነማን ይሆኑ የሚል ግፊት ይወተውተኝ ገባ እናም ድረገፁን ጠቅ ጠቅ በማድረግ ሳፈላልግ የእነማንን ሥም እንዳገኘሁ ይኼኔ ሳትገምቱ አትቀሩም ከረዥሙ ስም ዝርዝር ውስጥ ጥቂቱን እንካችሁ:-

1 ዶ/ር ነገዶ ጎበዜ
2 ዶ/ር ብርሃኑ ነጋ
3 ዶ/ር አረጋዊ በርሄ
4 ዶ/ር አበባ ፈቃደ
5 አቶ አያለው ማንደፈሮ (የደርግ የመከላከያ ሚኒስትር የነበሩ)
6 አቶ ፈቃደ ሸዋቀና
7 አምባሳደር እምሩ ዘለቀ (በዓፄ ኃይለስላሴ ዘመን አምባሳደር)
8 አቶ አበበ በለው
9 አቶ አብርሃ በላይ
10 የተከበሩ ወ/ሮ አና ጎሜዝ (ሃና ጎበዜ)

ይገኙባቸዋል:: በሰዎቹ መሃል አንድነትና ልዩነት ይታያችኋልን? ምን አንድ አደረጋቸውን? ለምን በአሁኑ ወቅት በሰፊ የፀረ ኢትዮጵያ ግንባር ሥር ተሰልፉ? ከዚህ አጠቃላይ ሴራ በስተጀርባ በአይዞህ ባይነትና በአዝማችነት የቆሙት የለየላቸው ፀረ-ኢትዮጵያ ኃይሎችና የኢትዮጵያን ሕዝብ ሰላም፣ ዲሞክራሲያዊና ፍትሃዊ አንድነት እንዲሁም የሕዝቦችና የብሄር ብሄረሰቦች የተመጣጠነ ሁለንተናዊ ልማት እኩልነት መቀበል የሚተናነቃቸው ወገኖች በአሁኑ ወቅት ለምን ሰልፋቸውን በአንድ ላይ አቀናጁ? መልሱን ለእናንተው የአእምሮ ጂምናስቲክ እተወዋለሁ::

ነገር ግን የኢትዮጵያን ሕዝብና ሃገሪቱን በደመኛ ጠላትነት ፈርጀው በሕዝቡ የልማትና የለውጥ ግስጋሴ ላይ አንዳች ሳንካ ለመፍጠር እንዲህ የሚያንጨረጭራቸው ምክንያት ምንድነው ለሚለው መልሱ ሳይቃጠል በቅጠል እንዲሉ ወይንም እች ባቂላ ያደረች እንደሆነ አትቀረጠምም ከሚል ስጋት በመነጨ ዓለማችን ዛሬ ነው:: ሕዝቡ አንገቱን እያቃና ባለበት በአሁኑ ወቅት አንገቱን ካላስደፋነው ስንቋምጥለት የነበረውን በሥልጣን ኮርቻ ላይ ተፈናጠን ሕዝቡን የመርገጥ የማስገበርና የመጨቆን ሕልማችን እንደ ጉም በኖ ይቀራል ከሚል የዋህ አስተሳሰብ የሚነሳ ይመስለኛል::

አያያዙን እያዩት ነው፤ በዛሬይቱ ኢትዮጵያ ከሚኖረው 80 ሚልዮን ሕዝብ 24 ሚልዮኑ በትምህርት ገበታ የሚውል የነገን ጠንካራ ኢትዮጵያ በዕውቀት ላይ የተመሠረተ ዘመናዊ ጎዳና ላይ የሚያራምድ ትውልድ ነው:: በዛሬይቱ ኢትዮጵያ የሕብረተሰቡ ግማሽ አካል የሆኑት ሴቶች ፖለቲካዊና ኢኮኖሚያዊ መብቶቻቸውን እኩል አስከብረው በሃገሪቱ ሁለንተናዊ ልማት ተዋናይ የሆኑበት ሁኔታ ተፈጥሯል:: ዛሬ ኢትዮጵያ ሃገራችን በአማካይ 50 ዓመት ዕድሜ ያለው ሕብረተሰብ የሚኖሩባት ሃገር ሆናለች:: በወሊድ ሕፃናት በሞት የሚቀጠፉባት የትላንቷ ኢትዮጵያ ገፅታ ተቀይሮ ዛሬ ከ1000 ሺህ የሚወለዱ ሕፃናት 700 ቶዎቹ የማደግ ዋስትና የተረጋገጠባት ሃገር ሆናለች:: ዛሬ ኢትዮጵያ በአንደኛ ደረጃ ትምህርት ከ90% በላይ ልጆቿ የትምህርት ማዕድ የሚቋደሱባት ሃገር ሆናለች::

ከሃያ ዓመታት በፊት በሃገራችን ሁለት ዩኒቨርሲቲዎች የነበሩበት ገፅታ ተቀይሮ የመንግሥት ብቻ ሃያ አንድ ዩኒቨርሲቲዎች በመላ ሃገሪቱ በመቶ ሺዎች የተቆጠሩ ወጣቶች የሚምነሸነሹባቸው ተቋማት ሆነዋል:: ከሁለት ዓመታት በኋላም አሁን ግንባታቸው በመካሄድ ላይ የሚገኙት 10 ዩኒቨርስቲዎች ተጨማሪ የዕውቀት መታደሚያ ሥፍራዎች ይሆናሉ::

ዛሬ የኢትዮጵያ ብሄር ብሄረሰቦች በአፍ መፈቻ ቋንቋቸው ትምህርት የሚያገኙ ብት ሁኔታ ተፈጥሯል:: ዛሬ ሁሉም ክልሎች የፌዴራላዊ ሕገመንግሥቱ ትሩፋትና ፀጋ የሆነውን ያልተማከለ አስተዳዳር ባለቤቶች በመሆን ፍርድ በየደጃቸውና መብት በእጃቻቸው መዳፍ ሥር ጨብጠዋል:: ዛሬ ሃገራችን ኢትዮጵያ ነዳጅ አልባ ከሚባሉት የአፍሪካ አገራት ከደቡብ አፍሪካ ለጥቃ በሁለተኛነት የተመዘገበ የኢኮኖሚ መሠረትና ዕድገት ያሳየች ጠንካራ ገስጋሽ አገር ሆናለች:: ሃገራችን ኢትዮጵያ በዓለም ባለፉት ተከታታይ ስድስት ዓመታት ባለ ሁለት አሃዝ ዕድገት ካስመዘገቡት አምስት ምርጥ ሃገሮች መካከል አንዷ ሆናለች::

በትላንቷ ኢትዮጵያ ጨርሶ ያልነበሩ አሥራ ሦስት የግል ባንኮች በትላንትናዋ ኢትዮጵያ ጨርሶ ሊታሰብ የማይችል ወደ 100 ቢልዮን ዶላር የግል ኢንቨስትመንት የሚላወስባት ሃገር ሆናለች:: የዛሬይቱ ኢትዮጵያ ባለፉት ጥቂት ዓመታት ብቻ የሦስት ግዙፍ የሃይል ማመንጫ መናሃሪያ በመሆን የሃይድሮ ኤሌክትሪክ ማመንጫ ኃይል ባለቤት ስትሆን ከሁለትና ሦስት ዓመታት በኋላም የግልገል ግቤ 3, 4 እና 5 ግዙፍ የኃይል ማመንጫ ማዕከላት እመቤት ትሆናለች::

ከሃያ ዓመታት ባነሰ ጊዜ በዓለም በአማካይ ገቢ ከተሰለፉት ሃገሮች ተርታ በመገኘ ት የሕዝቦቿን ሁለንተናዊ ዕድገት በማረጋገጥ እስከ ወዲያኛው እየተንደረደረ ወደፊት በመገስገስ የኢኮኖሚ ምህዳር ውስጥ ገብታ ያለፈው አኩሪ ታሪክዋ፣ አንፀባራቂ የሕዝቦቿ የነፃነት ቀናኢነት፣ ቅርስና አስመኪ ተጋድሎዋ እንዲሁም በዓለም የተመሠከረላት የሰው ልጅ እምብርትነትዋና የሥልጣኔ መገኛ ማህፀኗ በአዲሱ የዲሞክራሲ የመልካም አስተዳደርና የሕዝቦቿ ሁለንተናዊ የልማት ውጤት አምሮ ደምቆና አሸብርቆ የሚታይ ታፍራና ተከብራ የምትኖር ሃገር የምትሆንበት ወቅት ከአነጋገር ይፈረዳል ከአያያዝ ይቀደዳል እንዲሉ የሕዝቦቿ የለውጥ ውሳኔና የማይቀለበስ ጉዞ እየተመለከተ የሕዝቡ ታሪክ ሠሪነት ከቶውኑ የማይዋጥላቸው ጥቂቶች ጊዜው አሁን ነው በማለት በቀቢፀ ተስፋ ቢያሰፈስፉ ሊገርመን አይገባም የነብርን ጭራ አይዙም ከያዙም አይለቁም ብሎ በቁርጠኝነት በመነሳት የፈጣን ልማት ጭራን አይዙም ከያዙም አይለቁም ብሎ በመገስገስ ያለን ሕዝብ ምንም ዓይነት ምድራዊ ሃይል ሊመልሰው አይችልምና የአዛኝ ቅቤ አንጓች አስመሳይ ጭምብላችሁን አውልቃችሁ እርማችሁን አውጡ እንላቸዋለን:: በቸር ይግጠመን!!